CALGARY POLICE SERVICE

**የግል መረጃ ለመፈለግ እና ለማሳወቅ ስምምነት(ክፍል (1) አማርኛ**
**Amharic አማርኛ**

**የተስማሙበት ቀን**

**ፒዲኤፍ ኖቬምበር**

## የካልጋሪ ፖሊስ ኣገልግሎት

እኔ --------------------------- የካልጋሪ ፖሊስ አገልግሎት (“የፖሊስ አገልግሎት”) ስለእኔ የሚከተሉትን ምርመራዎች እንዲያደርግ እፈቅዳለሁ፡

ሀ  የወንጀል የፍርድ ውሳኔዎች ፣ ቅደመ ሁኔታ ያለባቸው እና ሙሉ በሙሉ የተሰረዙ እና ሌሎች ስለ እኔ በካናዳ ብሔራዊ የወንጀል ሪኮርድ መዝገብ ቤት ውስጥ የተካተቱ ተያያዥ መረጃዎች ።

ለ  የ ፐሮቪንስ እና የወንጀል ድንጋጌ የፍርድ ውሳኔዎች እና ኣልበርታ ፍርድ ቤት በሂደት ላይ ያለ ክስ ጀስቲስ ኦንላይን ኢንፎርሜሽን ኔትወርክ ላይ እንደተገለጸው

ሐ.  በወቅቱ ያሉ የፍርድ ቤት ትዕዛዞች ፣ የእስር ትዕዛዞች ፣ የእግድ ትዕዛዞች ፣ የኣመክሮ ትዕዛዞች ፣ የዋስ ቅድመ ሁኔታ ማስያዣዎች ፣ በአልበርታ የሚገኙ የ ዋስ ማስያዛዣ ትዕዛዞች እና በካናዳ የፖሊስ መረጃ ማዕከል ውስጥ የተጠቀሱ በወቅቱ የሚገኙ ከ ፐሮቪንሱ ውጭ ያሉ የ እስር ትእዛዞች

መ  ከአከባቢው የፖሊስ መዝገቦች የተገኘ መረጃ ፣ ይህም የፖሊስ መረጃ ፖርታል ኣሰሳን ሊያካትት ይችላል ፣ በዚህ ውስጥ ለህዝብ ደህንነት ስጋት የሆነበት ጉዳይ ተብሎ የፖሊስ ምርመራ የተደረገብኝ ። እዚህ በክፍል መ የተገለፀውን መረጃ ለመግለጽ ውሳኔው የተጠየቀውን የሥራ ቦታ ኃላፊነት ምንነት ፣ የምገናኛቸውን ግለሰቦች ፣ የክስተቶች ድግግሞሽ እና የጊዜቅርበት ፣ ማንኛውም የታዩ የባህሪ ተደጋጋሚነቶች እና በመዝገቦቹ ውስጥ የተካተቱት መረጃዎች አስተማማኝነት ።

 **ለአደጋ ተጋላጭ የሆኑ ጋር ለሚሰሩ ዘርፍ ምርመራ፡** በአመልካች ኤጀንሲ ሲጠየቅ ሙሉ ይሆናል፡ ምክንያቱም እርስዎ ለህጻናት ፣ ለአረጋውያን ፣ ለአካል ጉዳተኞች ወይም ለሌሎች ተጋላጭ ለሆኑ ህብረተሰብ ደህንነት ተጠያቂ ይሆናሉ ። እርስዎ የሚያመለክቱበት ቦታ ለጥቃት ተጋላጭ ለሆኑ የዘርፉ የፖሊስ ምርመራዎች መስፈርቶችን የሚያሟላ መሆኑን የሚወስነው ወይም የሚያረጋግጠው የፖሊስ አገልግሎት ነው ።

ተጋላጭ የሆነ የዘርፍ ምርመራ የሚያስፈልገው አካል ጉዳተኞችን ጨምሮ ተጋላጭ ለሆኑ ሕፃናት እና፣ አረጋውያን  ጋር በሃላፊነት ዕና እምነት ተጥሎብዎት በሚሰሩበት ጊዜ ነው ። ተጋላጭ የሆነ ዘርፍ ምርመራ የወንጀል ሪኮርድን ወይም ይቅርታ የተደረገለት የወሲብ ጥፋተኛ) በ ኣርሲኤምፒ የተያዘ ሬከርድ የማውጣት የወንጀል ሪኮርድን (ይቅርታ የተደረገለት ወይም ረከርዱ የታገደ የወሲብ ወንጀል አድራጊ መኖሩን ለማረጋገጥ) የሚደረግ መልሶ ማግኛ ስርዓትን ያካትታል ። ተጋላጭ የሆነ ዘርፍ ምርመራ ተጋላጭ በሆነ ሰው ላይ ጉዳት የሚያስከትሉ ማንኛውም ተደጋጋሚ ባህሪዎች መኖራቸውን ለማወቅ የአከባቢውን የፖሊስ መዝገቦች መመርመርን ያካትታል ።

• የፖሊስ መዝገብ በፖሊስ የተፈጠረ ወይም የተሰበሰበ መረጃን የያዘ ነው ። እሱ እንደ የወንጀል ክሶች እና ጥፋተኝነት ውሳኔዎች ፣ነፃ የመሆን ለምሳሌ ያለመከሰስ መረጃ ፣ በአእምሮ መታወክ ምክንያት በወንጀል ተጠያቂ ያለመሆን ሁኔታዎች ፣ የፍርድ ሂደቱን መቆየት ፣ በአማራጭ ሁኔታዎች እና በሌሎች የውሳኔ ሂደት ማዘዋወር ፕሮግራሞች ተሳትፎ ፣ የ ወንጀል ክስ ያልተመሰረተባቸው ምርመራዎች እና ክስተቶችን ሊያካትት ይችላል ። የፖሊስ መዝገብ እንዲሁ ከፖሊስ ጋር የወንጀል ያልሆነ ግንኙነትን ሊያካትት ይችላል ። ምንም እንኳን በጭራሽ ተከስሰው ወይም በወንጀል ተከሰው ባያውቁም እንኳ በአእምሮ ጤና ጉዳዮች ምክንያት የሚደረጉ ግንኙነቶችን ወይም እርስዎ ኣውቀውም ይሁን ሳያውቁ በፖሊስ በተደረገ ምርመራ ምክንያት የፖሊስ ሪከርድ ሊኖር ይችላል ። በፖሊስ የተፈጠረ ወይም የተሰበሰበው መረጃ በፖሊስ አገልግሎት መዝገቦች ማቆያ መርሃግብር መሠረት ይቀመጣል ። ስለ ፖሊስ አገልግሎት ማቆያ የጊዜ ሰሌዳ ተጨማሪ መረጃ ከፈለጉ እባክዎን የፖሊስ መረጃ ምርመራዎን የማድረግ ኃላፊነት ያለበትን የፖሊስ አገልግሎት ያነጋግሩ።

---

የፖሊስ አገልግሎት ከእኔ ተጨማሪ ፈቃድ ሳይኖር ይህን መረጃ ለአመልካች ኤጀንሲ እንደማይሰጥ እገነዘባለሁ ።

☐ ለአደጋ ተጋላጭ ዘርፍ የፖሊስ ምርመራ በሚፈለግበት ጊዜ ፣ አስፈላጊ ከሆነም ለአደጋ ተጋላጭ ለሆኑት ዘርፎች ምርመራ ተስማምቻለሁ ።

በወንጀል ሪኮርዶች ሕግ መሰረት በተዘረዘሩት የወሲብ ነክ ወንጀሎች በወንጀል ተከስሼ ከሆነ ለተከሰስኩበት ወንጀልም ምህረት አግኝቼ እንደሆነ በ አርሲኤምፒ የተያዘ ሬከርድ የማውጣት የወንጀል ሪኮርዶች መልሶ ማግኛ ስርዓት ውስጥ በሚደረግ ምርመራ እንዲፈቀድ ተስማምቻለሁ ።

ይህንን ስምምነት በመሰጠቴ ምክንያት ምህረት ከተሰጠበት ወይም ከተሰጠበት የወንጀል ሪኮርዶች ሕግ  ውስጥ ከተዘረዘሩት የወሲብ ጥፋቶች መካከል በአንዱ ጥፋተኛ መሆኔን የሚያሳይ መዝገብ ካለ  ፣ ያንን  መዝገብ ኣርሲኤምፒ ለካናዳ ጠቅላይ አቃቤ ህግ ይሰጣል ፣ ከዚያ በዚያ መዝገብ ውስጥ የተገኘውን መረጃ በሙሉ ወይም በከፊል ለፖሊስ ኃይል ወይም ለሌላ ስልጣን ላለው አካል ሊገልጽ ይችላል ። ያ የፖሊስ ኃይል ወይም የተፈቀደለት አካል ያንን መረጃ ለእኔ ይገልጻል።

---

☐ የፖሊስ መረጃ ምርመራውን ለማጠናቀቅ ከአካባቢው የፖሊስ መዝገብ የተገኘውን መረጃ ጨምሮ ከላይ የተገለጹትን ምርመራ ካጠናቀቀ በኋላ ያገኘውን ስለ እኔ ማንኛውንም እና ሁሉንም መረጃ እንዲጠቀም እና የፍተሻዎቹን ውጤቶች በፖሊስ መረጃ ምርመራ ውስጥ ለእኔ እንዲያሳውቀኝ  ፈቃዴን ለፖሊስ አገልግሎት እሰጣለሁ  ።

የምርመራዎቹን ውጤቶች ለሌላ ሰው ወይም ድርጅት መስጠት የኔ ውሳኔዬ እንደሆነ ተረድቻለሁ ። ስለ ፖሊስ መረጃ ፍተሻ ሂደት ተጨማሪ መረጃ በፖሊስ አገልግሎት ድርጣቢያ ላይ በሚገኘው የአልበርታ የፖሊስ መረጃ ፍተሻ ሂደቶች ውስጥ እንደሚገኝ ተረድቻለሁ

---

☐ ይህንን ፎርም በመፈረም ወይም የኤሌክትሮኒክ ስምምነት በመቀበል ፣  ሙሉ መረጃ እንዳገኘሁ እና የዚህ ስምምነት እና ከኃላፊነት የመላቀቅ ይዘት ፣ ትርጉም እና ውጤት እንደተረዳሁ አረጋግጣለሁ እናም እኔ የሰጠሁት መረጃ ትክክለኛ መሆኑን እና አስፈላጊ ከሆነ  በፖሊስ አገልግሎቱ በፖሊስ መረጃ የመረጃ ቋቶች በኩል ማረጋገጥ ይቻላል ።

ተቀብያለሁ ☐ ቀን

የፖሊስ አገልግሎትን ፣ የፖሊስ አገልግሎት የፖሊስ አዛዥ ፣ የፖሊስ አገልግሎት የፖሊስ ኮሚሽን እና አስተዳዳሪዎቻቸው ፣ ተተኪዎቻቸው ፣ ለተተኪዎቻቸው ፣ ለሾሚቻቸው ፣ ለተወካዮቻቸው ፣ ለኦፊሰሮቻቸው ፣ ለኣገልጋዮቻቸው ፣ ለሰራተኞቻቸው እና ለሰራተኞቻቸው ከማንኛውም እና ከማንኛውም የህግ ጥያቄ ወይም  ሃላፊነት ጥያቄ ውስጥ እንዳይገቡ ከሃላፊነት ነጻ ኣደርጋለሁ ለዘላለምም ከዚ ሃላፊነት ነጻ ኣደርጋለሁ፡፡ሁሉንም ይዘት ያለው እና ዓይነት እና በፖሊስ መረጃ ፍተሻ ሂደት ውስጥ ከመሳተፌ እና የፖሊስ መረጃ ፍተሻ ከማግኘት ጋር በተያያዘ በማንኛውም መንገድ የተነሱ  እኔ ወይም በሕጋዊ ወኪሎቼ ፣ ወራሾቼ ፣ ተወካዮቼ የተከሰቱ ሁሉንም ዓይነት ድርጊቶች ፣ ክሶች ፣ ዕዳዎች ፣ ግዴታዎች ፣ አጠቃላይ ጉዳቶች ፣ ልዩ ጉዳቶች ፣ የገንዘብ ጉዳቶች ፣ ወጭዎች ወይም ወለድ ያለ ገደብ ያለ ሕግ ፣ ወይም በፍትሃዊነት ጉዳይ ከሃላፊነት ነጻ ኣደርጋለሁ።

በዚህ ቅጽ ላይ የተሰበሰበው መረጃ እና የዚህ የፖሊስ መረጃ ማጣሪያ ሂደት አካል ሆኖ የተሰበሰበው እና የተገለፀው መረጃ በመረጃ ነፃነት እና የምስጢራዊነት ጥበቃ ህግ መሠረት ወይም በሌላ መልኩ በሕግ በተደነገገው መሠረት ይሰበሰባል ፣ ይፋም ይደረጋል።

CALGARY POLICE SERVICE

# የፖሊስመረጃ ምርመራ

## የግል መረጃ ለመፈለግ እና ለማሳወቅ ስምምነት(ክፍል (1)

PO 1244 (R2014-11)

A. **የኣመልካቹ መረጃ**

እባክዎ በሰማያዊ እስክሪብቶ ግልጽ ኣድረገው ይጻፉ እና ሙሉ በሙሉ ያጠናቁ

| | | |
|---|---|---|
| **1) አሁን ያለዎት የአያት ስም:** | | |
| **ስም** | **የኣባት ስም** | **ተለውጭ/ቅጽል ስም/የሚመርጡት ስም** |

**2) ሌላ ስም ተጠቅመው ያውቃሉ?**
የትውልድ, የጋብቻ, የቀድሞወይም በህግ የተቀየረ ስም?
□ **የለም** □ **አዎ**
**አዎ ካሉ ሌላ ስም እዚ ስር ያስፍሩ**

________________________________________

________________________________________

**3) የትውልድ ቀን**
አ.ም | ወር | ቀን

**4) ጾታ**
□ ወንድ □ ሴት

**5) የትውልድ ስፍራ** ከተማ / ፕሮቪንስ/ግዛት / ኣገር)

**6) ስልክ ቁጥሮች** **የቤት** ( )
**የስራ** ( ) **ሞባይል** ( )

**7) ካልጋሪ ውስጥ ምን ያህል ጊዜ ኖረዋል?**

**ከአንድ አመት በታች ከሆነ,ከዚያ በፊት የት ነበር የሚኖሩት?**

**8) የአሁኑ የመኖሪያ አድራሻዎ**
የአፓርትመንት ቁጥር እና የጎዳና አድራሻ
ከተማ / ከተማ አውራጃ የፖስታ ኮድ

**9) የፖስታ አድራሻዎ (የተለየ ከሆነ)**
የአፓርትመንት ቁጥር እና የጎዳና አድራሻ
ከተማ / ከተማ አውራጃ የፖስታ ኮድ

**10) ይህ የፖሊስ ምርመራ የሚያስፈልገው ለ**
□ ስራ □ በጎፍቃድ □ ጉዲፈቻ □ ኢሚግሬሽን
□ ሌላ (ያብራሩ) ____________________
(ለ የትኛው መስሪያ ቤት) ____________________

**11) የፖሊስ መረጃ ምርመራው ለስራ ወይም ለበጎ ፍቃድ ከሆነ – እባክዎ የስራ ዝርዝር ያቅርቡ. ለሌላ ኣላማ ከሆነ ምክንያቱን ይግለጹ**

**12) የስራላይ ልምምድ**
□ በክፍያ □ ያለክፍያ
□ ትምህርትቤቱን ይግለጹ ____________________

**13) የምሰራውወይም የበጎፍቃድ የማደርገው :**
□ አካልጉዳተኞች □ ልጆች/ወጣቶች
□ አዛውንት □ ህሙማን □ አይመለከተውም

**ለሲፒ ኤስ ብቻ**
**VS**

**14) ካናዳ ወስጥ ለተፈፀመ የወንጀል ጥፋት ( ምህረት የተደረገልዎ እና ሬከርዱ ይፋ እንዳይሆን ለተባለልዎት )አሻራ ሰጥተው ያውቃሉ?**
□ **አይ** □ **አዎ**

የተሰጠው መረጃ ትክክል ነው
የአመልካች ፊርማ ____________________
የተፈረመበት ቀን | አመት | ወር | ቀን

**(የፖሊስ ፅህፈት ቤት ሰራተኛ ወይም የኤጀንሲ ሰው ጋር ከመድረሱ በፊት ይፈርሙt)**

**B, በ ድርጅቱ ብቻ የሚሞላ ክፍል**
*ይህ ፎርም በድርጅቱ የሚላክ ከሆነ የአመልካቹን መታወቂያ ማካተት አለበት

| የድርጅቱ ስም | የድርጅቱ አድራሻ(ይፃፉ) | የድርጅቱ ታዛቢ (ይጻፉ) |
|---|---|---|

**ቮለንተር አልበርታ(VOAN) ቁጥር**
(በጎ ፍቃድ የሚሰራለት ድርጅት ፍቃድ ቁጥር)

## ከዚህ መስመር በታች ኣይጻፉ –ይህ ስፍራ ለ ካልጋሪ ከተማ ብቻ ነው

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ያመለከቱበት የስራ ዘርፍ | | ክፍል | | የስራ ክፍል | |
| ጠቅላላ ቢዝነስ ክፍል | አካውንት | ፈንድ | ዲፓርትመንት ኣይ ዲ | እንቅስቃሴ | ሬፈረንስ |

## ከዚህ መስመር በታች ኣይጻፉ –ይህ ስፍራ ለ ካልጋሪ ፖሊስ ብቻ ነው

መረጃው የተወሰደው በ__________: _______________ □ የኣደጋ ተጋላጮች ዘርፍ ምርመራ ተጠናቋል ኣመልካቹ ምርመራ የተደረገበት:

| ሲፒአይፒ፨/ፒኢአርኤስ/ሲኤን አይ | ተቀላቀል/ በሂደት ላይ ያለ | ፒአይኤም ኤስ |
|---|---|---|
| | | |

አሻራ